2/ የችግሩ መግለጫ P roblem Statement

ከከተሞች መስፋፋትና የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ፣ የአምራች እና አገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪዎች በመስፋፋት ላይ ይገኛሉ። የእነኚህ ማህበራዊ ፐብሊክ ተቋማት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪዎች እየተስፋፉ መምጣታቸዉ በከተሞቹ ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ ለሚደረገዉ ጥረት የሚጫወቱት አዎንታዊ ሚና ባሻገር በሰዎችና እንስሳት ጤና ብሎም በኤኮሎጂ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ከፍተኛ መጠን ያለዉን አደገኛ ቆሻሻ ምርት አስተዋጽኦ ማበርከቱን ጥናቱ አረጋግጧል።

በእርግጥ በሰዉና እንስሳት ጤና፣ በኤኮሎጂ እና በከተሞች ንጽህና እና ዉበት አደጋ የደቀኑ የተለያዩ አደገኛ ቆሻሻዎች(መርዛማ ኬሚካሎች፣ ሹልና ስለታማ ቁሳቁሶች፣ ብረታብረቶች ወወተረፈ)መጠን መጨመር የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ቁጥር መጨመር የትምህርትና የጤና ተቋማት፣ የአገልግሎት ሰጪ እና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መስፋፋት ተጠባቂ /ተፈጥሯዊ ዉጤት ሳይሆን በከተሞቹ ዘመናዊና ዉጤታማ የቆሻሻ ማኔጅመንት (የቆሻሻ ልየታ(Waste segregation) ሕክምና(waste treatment)፣ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም(waste recycling )፣በጣም ዝቅተኛ በመሆኑና ብዙ ቆሻሻ አደገኞችን ጭምር የሚያመርቱ ተቋማት ኃላፊነት በጎደለዉ ሁኔታ ቆሻሻን በክፍት ቦታዎች ወንዞችና ጅረቶች የሚጥሉ በመሆናቸዉ ነዉ።

3. ቁልፍ/ዋና ዋና ግኝቶች

3.1 በስድስቱም ከተሞች የቆሻሻ ምርት መጠን የጨመረ ሲሆን በየዓመቱ እጅግ በጣም ከፍተኛ መጠን ያለዉን ደረቅ ቆሻሻ (Highest amount of solid waste (305,400 kg/year) ዲላ ቀጥሎ ዎላይታ ሶዶ ዎላይታ ሶዶ በዓመት እጅግ በጣም ከፍተኛ ፈሳሽ ቆሻሻ (18.2 million liters/year) ያመርታል።

3.2 ዋነኛ የቆሻሻ አመንጪዎች (Major waste generators)

- የግልና የመንግስት/ፐብሊክ ጤና ተቋማት
- የግልና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች /ኮሌጆች
- ቄራዎችና የመኪና ዕጥበት ማዕከላት
- በአጠቃላይ እነኚህ ተቋማት በከተሞቹ በዓመት ከሚመረተዉ ቆሻሻ ከ60% በላይ ያመርታሉ።

3.3 የቆሻሻዉ ይዘት (Nature of Waste)

በስድስቱ ከተሞች በየዓመቱ ከሚመነጨዉ አጠቃላይ የቆሻሻ መጠን ዉስጥ አደገኛ ቆሻሻ 71% ነዉ። መርዛማ ኬሚካሎች (50%)፤ ሹልና ስለታማ ቁሳቁሶች፣ የዛጉ ብረታብረቶች፣ የላቦራቶሪና ሕክምና ቅሪቶች እና ሌሎች አደገኛ ቆሻሻዎች(21%) መሆናቸዉን ጥናቱ አመላክቷል።

3.4 የቆሻሻ ማኔጅመንት ልምድ (Waste Management Practices)

- ከዋነኛ የቆሻሻ አመንጪ ተቋማት መካከል አብዛኛዎቹ ምቹ(safe) ጊዜያዊ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ የላቸዉም። *ለአብነት በጂንካ ከተማ ጊዜያዊ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ የለም።
- በቆሻሻ ምንጭ ሥፍራ የቆሻሻ ልየታ(Waste segregation) ተግባር በጣም ዝቅተኛና ወጥነት የጎደለዉ ነዉ።

- በጣት የሚቆጠሩ ተቋማት ብቻ ቆሻሻን ከማስወገዳቸዉ በፊት ተገቢ የቆሻሻ ሕክምና (waste treatment) ያደርጋሉ።
- በጣም አብዛኞቹ ተቋማት ቆሻሻን ጥንቃቄ በጎደለዉ መንገድ ያዳዳዛሉ፤ በክፍት ሥፍራዎች፣ወንዞችና ጅረቶች ይጥላሉ።

3.5 አሉታዊ አንድምታዎች (Impacts)

1/በቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች እና ኃላፊነት በጎደለው ሁኔታ ቆሻሻ በሚጣልባቸዉ አከባቢዎች የሚኖሩ ሕዝቦች ለተለያዩ በሽታዎች- የዉሃ ወለድ እና አስም ለመሳሰሉ የመተንፈሻ አካል ሕመሞች ተጋልጠዋል። (Communities face rising health risks (respiratory illness, infections, toxic exposure).

2/ የአከባቢ/ኤኮሎጂ ብክለት/ጉዳት

- የዉሃ የአፈርና የአየር ብክለት
- የብዝሃ ሕይወት መመናመን

3/ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት

የምርታማነት መቀነስ፣ የማህበረሰብ ኑሮ ደረጃ መላሸቅ፣ በየስፍራዉ የተጣለዉ ቆሻሻ እና መጥፎ ሽታ የከተሞችን ንጽሕና እና ዉበት(sanitation and aesthetic value) መቀነስ)

3.6 ዋና ዋና መንስኤዎች

1/ የአከባቢ ጥበቃ እና የቆሻሻ አወጋገድ መመሪያዎች የማስፈጸም ሥርዓት እጅግ ደካማ መሆን

2/የቆሻሻ ማኔጅመንት - የቆሻሻ መጠን መቀነስ(waste reduction)፣ልየታ( waste segregation) የቆሻሻ ሕክምና/ማጥሪያ(waste treatment)፣ቆሻሻን መልሶ መጠቀም(Waste recycling )ወዘተርፈ ቴክኖሎጂና መሠረተልማት ከፍተኛ ዉስንነት/ዕጥረት

3/የቆሻሻ ዋነኛ አመንጪ ተቋማት ብሎም የማህበረሰቡ ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን

3.7 የፖሊሲ አንድምታ (Policy Implications)

ጥንቃቄ ለጎደለዉ የአደገኛ ቆሻሻ አወጋገድ ልምምድ ዋና ዋና መንስኤዎችን ዉጤታማና ዘላቂ በሆነ መንገድ መቅረፍ ካልተቻለ በፐብሊክ ጤና፣ በኤኮሎጂ/አከባቢ፣ ብዝሃ ሕይወት፣ በከተሞች ዘላቂ ልማት እና አጠቃላይ ሕልዉና ላይ ከፍተኛ/ከባድ ስጋት

ያስከትላል።

4/ ሊተኮሩ የሚገባቸዉ የፖሊሲ ዕርምጃዎች /ምክረ ሐሳቦች( TARGETED POLICY ACTIONS /RECOMMENDATIONS )

I/ ከክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚጠበቁ የፖሊሲ እርምጃዎች

የኢንቨስትመንት ፍቃድን ከአካባቢ ደንብ ተግባራዊነት ጋር ማገናኘት

ሀ. የተቀናጀ ክልላዊ የቆሻሻ ማኔጅመንት ሥርዓት መዘርጋት

ለ/ በካቢኔ ደረጃ የሚመራ ክልላዊ የአደገኛ ቆሻሻ ማኔጅመንት ግብረሃይል መመሥረት

ሐ/የአከባቢ ጥበቃ እና የከተማ ንጽህናና ዉበት መመሪያዎችን/ደንቦች ማስፈጸም

መ/ ነባር የአከባቢ ጥበቃ እና የከተማ ንጽሕናና ዉበት አጠባበቅ መመሪያዎችና ደንቦች ጥብቅ አስገዳጅነት ማረጋገጥ

ሠ/ ኃላፊነት-ጥንቃቄ በጎደለዉ ሁኔታ ቆሻሻን ባጠቃላይ አደገኛ-መርዘኛ ቆሻሻ በተለይ የሚያጠራቅሙ እና የሚጥሉ ተቋማት ላይ ተገቢ ቅጣት የሚወሰድበትን ደንብ/መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ

3. ለዘመናዊ -ዉጤታማ የቆሻሻ ማኔጅመንት መሠረተ ልማትና ቴክኖሎጂ ላይ በቂና ተገቢ በጀት መመደብ/

በከፍተኛ ስጋት ዉስጥ ለሚገኙ የዲላ እና ዎላይታ ሶዶ ከተሞች ቅድሚያ ትኩረት መስጠት (Prioritize funding for high-risk cities (e.g., Wolaita Sodo, Dilla)

4. የክልል የቆሻሻ አስተዳደር ስትራቴጂን መንደፍ፣ ማፅደቅና ተግባራዊ ማድረግ

5/የክልል የአደገኛ ቆሻሻ አስተዳደር ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣ በክልል የልማት እና የከተማ እቅድ ማዕቀፎች ውስጥ ማካተት

ii. ለክልል  ቢሮዎች የሚመከሩ የፖሊሲ እርምጃዎች

1. የከተማ ልማትና መሠረተ ልማት ቢሮ እና ከተማ አስተዳደሮች

- የተቀናጀ የቆሻሻ መሰብሰብና መጓጓዣ ስርዓት ማቋቋም
- የመሠረታዊ መርሀ ግብር የተመሠረቱ የቆሻሻ መድብ (engineered landfill) እና የመለዋወጫ ጣቢያዎች (transfer stations) መገንባት
- በምንጩ የቆሻሻ መለያየትን (waste segregation) አስገዳጅ ማድረግ
- ለቆሻሻ አገልግሎት የተጠቃሚ ክፍያ (user fees)
- በአደገኛ ቆሻሻ አመንጪዎችን የአካባቢ ግብር ወይም ክፍያዎች (levies) ማስከፈል
- ለአደገኛ ንጥረ ነገሮች ዳግም ጥቅም ማዋልና ማስመለስ (reuse) እንቅስቃሴዎችን መደገፍ
- አደገኛ ቆሻሻን በአጠቃላይ የከተማ ሳኒቴሽን ስርዓቶች ውስጥ ማካተት
- የቆሻሻ መቀነስና ዳግም ጥቅም ማዋል ማበረታታት
- ማዕከላዊ የአደገኛ ቆሻሻ ማስተናገድ ፋሲሊቲዎችን መቋቋም
- የኢንስፔክሽን ደንቦች ማስፈፀምና ተግባራዊነት ማረጋገጥ

2. የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን

- የምርመራና የተግባራዊነት (compliance) ክትትል ስርዓቶችን ማጠናከር
- በኢንዱስትሪዎችና ተቋማት ላይ የመደበኛ የአካባቢ ኦዲት (environmental audit) ማካሄድ
- የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ (EIA) አፈፃፀምን ማስኬድና ማስፈፀም

- ለዳግም ጥቅም ማዋል (recycling) እና የቆሻሻ ማስተናገድ ኢንቨስትመንቶች የሚያበረታቱ እንቅስቃሴዎችን/ኢንሰንቲቮች መፍጠር

3. የጤና ቢሮ

የህክምና/ላቦራቶሪ ቆሻሻ አስተዳደር ደንቦችን በጥብቅ ማስፈፀም

4/በሁሉም የጤና እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቆሻሻ ማስወገጃ መሳሪያዎች (ለምሳሌ፡ ኢንሲነሬተሮች) እንዲጫኑ ማድረግ

5. አቅም ማጎልበትና ግንዛቤ ማሳደግ

- የከተማ አስተዳደር ሰራተኞችን፣ የቆሻሻ አያያዞችን እና የግል ኦፕሬተሮችን ማሰልጠን
- ስለ አደገኛ ቆሻሻ አደጋዎች የህዝብ ግንዛቤ ዘመቻ

4. የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ

- የኢንቨስትመንት ፍቃድን ከአካባቢ ጥበቃ ደንብ ተግባራዊነት ጋር ማገናኘት
- ኢንዱስትሪዎች በቦታቸው የቆሻሻ ማስተናገድ (on-site treatment) ስርዓቶችን እንዲያውሉ መጠየቅ
- ንፁህ የምርት አሰራሮችን (cleaner production practices) ማበረታታት

5. የፋይናንስ ቢሮ

- ዘላቂ የፋይናንስ መሰብሰብ ተግባር ማረጋገጥ
- የመንግስት ድጋፍ (public funding)
- የህዝብና የግል ሽርክና (PPP) አቀራረቦች
- የዶነሮችና የልማት አጋሮች ድጋፍን መጠቀም
- መደምደሚያና አንድምታዎች

የአደገኛ ቆሻሻ ያልተገባ አስተዳደር ለህዝብ ጤና፣ ለአካባቢ ደህንነት እና ለዘላቂ የከተማ ልማት እየጨመረ የሚሄድ አደጋ ያመጣል። የተገቢ የፖሊሲ እርምጃ ካልተወሰደ ከተሞች የአካባቢ ብክለት፣ የበሽታ መጠን መጨመር እና ከአካባቢ ጉዳት የሚመጡ ኢኮኖሚያዊ ወጪዎችን ይቀጥላሉ።

ችተመከሩትን የፖሊሲ እርምጃዎች መፈጸም ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ተመጣጣኝ እና ዘላቂ የአደገኛ ቆሻሻ አስተዳደር ስርዓት ለመፍጠር ያስችላል። በረጅም ጊዜ፣ ይህ የጤና አደጋዎችን ያነሳል፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን ይጠብቃል፣ የከተማ ኑሮ ጥራትን ያሻሽላል እና የተቋማት አቅምን ያጠናክራል። በአጠቃላይ፣ ውጤታማ የአደገኛ ቆሻሻ አስተዳደር የተቋቋሙ ከተሞችን፣ የተሻለ የኑሮ ጥራትን እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ልማትን ይገነባል።

References

ICBPS(2024) Hazardous Waste Management Practices &Challenges in Selected Cities of Soutb Ethiopia Region (2024) Wolaita Sodo.